የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፰ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 8
ADDIS ABABA 6th January, 2014

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻/፳፻፮ ዓ.ም
የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲን ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..........ገጽ ፯ሺ፩፻፷፰

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻/፳፻፮

## የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፳፻፫ አንቀጽ ፭ እና በተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፱/፳፻፭ አንቀጽ ፳፱(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻/፳፻፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "አዋጅ" ማለት የተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን አዋጅ ቁጥር ፯፻፺፱/፳፻፭ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

፫/ "የመድን ፈንድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ መሠረት የተቋቋመው የመድን ፈንድ ነው፤

፬/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፭/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.10

## CONTENTS

Regulation No. 300/2013
Insurance Fund Administration Agency Establishment
Council of Ministers Regulation ....................Page 7168

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 300/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE INSURANCE FUND ADMINISTRATION AGENCY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2003 and Article 29(1) of the Vehicle Insurance Against Third Party Risks Proclamation No. 799/2013.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Insurance Fund Administration Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 300/2013".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Vehicle Insurance Against Third Party Risks Proclamation No. 799/2013;

2/ definitions provided under Article 2 of the Proclamation shall also apply to this Regulation;

3/ "Insurance Fund" means the insurance fund established by Article 19 of the Proclamation;

4/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Transport, respectively;

5/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

## ፫. መቋቋም

፩/ የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" እየተባለ የሚጠራ) የህግ የሰውነት መብት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኤጀንሲው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

## ፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፭. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ ስለመድን ፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

፪/ ለተሽከርካሪ አደጋ ተጎጂዎች በአዋጁ አንቀጽ ፳ መሠረት ካሳ ይከፍላል፤

፫/ በተሽከርካሪ አደጋ ምክንያት ለደረሰ ጉዳት ካሣ የተከፈለባቸውን የሞትና የአካል ጉዳት እንዲሁም የንብረት ውድመት መረጃዎች ይሰበስባል፤

፬/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የሚኒስቴሩን ፈቃድ በመጠየቅ የተወሰኑ ተግባራቱ አግባብነት ባላቸው ተቋማት በውክልና እንዲከናወኑ ያደርጋል፤

፭/ ለመድን ፈንዱ የተለየ የሂሳብ መዝገብ ይይዛል፣ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎችን ያዘጋጃል፤

፮/ ለመድን ሽፋን የምስክር ወረቀትና ተለጣፊ ህትመት ከፈንዱ ሂሳብ ወጪ በማድረግ እንዲታተም ያደርጋል፤ ለመድን ሰጪዎች ባሰራጨው መጠን የህትመቱን ወጪ በማሰባሰብ ወደ ፈንዱ ሂሳብ ተመላሽ ያደርጋል፤

፯/ የመድን ፈንዱን የፋይናንስ ምንጭ ለማጎልበት ከፈንዱ ክምችት ላይ ለመጠባበቂያ የሚይዘውን ቀንሶ ቀሪውን መንግሥት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ኢንቨስት ያደርጋል፤

፰/ ስለመድን ፈንድ ገቢዎችና አጠቃቀም፣ ስለተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን እና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች ወቅታዊ ህትመቶችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፤



## 3. Establishment

1/ The Insurance Fund Administration Agency (hereinafter the "Agency") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Agency shall be accountable to the Ministry.

## 4. Head Office

The Agency shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## 5. Powers and Duties of the Agency

The Agency shall have the powers and duties to:

1/ undertake study on the collection and disbursement of the Insurance Fund and implement same;

2/ pay compensation to vehicle accident victims in accordance with Article 20 of the Proclamation;

3/ collect data on deaths, bodily injuries and property damages caused by vehicle accidents with respect to which compensations have been paid;

4/ where necessary and upon obtaining the approval of the Ministry, delegate the appropriate institutions to perform some of its activities;

5/ maintain separate accounts and records for the Insurance Fund and prepare annual financial statements;

6/ print insurance certificates and stickers using the Insurance Fund; and collect and reimburse the cost to the Fund based on the quantities distributed to the insurance companies;

7/ invest, in order to strengthen the financial sources of the Insurance Fund, accumulated collections of the Fund remaining after deducting reserve pursuant to directive of the government ;

8/ prepare and distribute current publications on the collections and disbursements of the Insurance Fund, vehicle insurance against third party risks and other similar topics;

፱/ ከተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማካሄድ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፲/ አዋጁን እና አዋጁን ለማስተግበር የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያስፈጽማል፤

፲፩/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፲፪/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

፮. <u>የኤጀንሲው አቋም</u>

ኤጀንሲው፡-

፩/ የመድን ፈንድ ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ እና

፫/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

፯. <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩/ ቦርዱ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከመድን ኩባንያዎች የተውጣጡ በሚኒስትሩ የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፡፡

፪/ የቦርዱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

፰. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

፪/ ከተሽከርካሪ አደጋ የሦስተኛ ወገን መድን ሽፋን ጋር የተያያዙ የፖሊሲ ጉዳዮችን እና በአዋጁ አንቀጽ ፬(፬) እና አንቀጽ ፳፫(፪) መሠረት የሚቀርቡ የአረቦንና የመድን ፈንድ ተመን ጥናቶችን ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

፫/ ስለመድን ፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሁኔታ መመሪያ ያወጣል፤

፬/ በተሽከርካሪ አደጋ ጉዳት ደርሶባቸው በአዋጁ አንቀጽ ፳ መሠረት ተገቢው ካሣ አልተከፈለንም በማለት ቅሬታ የሚያቀርቡ ጉዳተኞችን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤



9/ undertake and present to the Ministry policy studies on issues related to vehicle insurance against third party risks, and implement same upon approval;

10/ implement the Proclamation and regulations and directives issued for the implementation of the Proclamation;

11/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

12/ carry out other related activities necessary for the realization of its objectives.

6. <u>Organization of the Agency</u>

The Agency shall have:

1/ Insurance Fund Board (hereinafter the "Board");

2/ a Director General and, as may be necessary, a Deputy Director General, to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

7. <u>Members of the Board</u>

1/ The Board shall be composed of members appointed by the Minister from the relevant governmental institutions and insurance companies.

2/ The number of members of the Board shall be determined as deemed necessary.

8. <u>Powers and Duties of the Board</u>

The Board shall have the powers and duties to:

1/ oversee and supervise the operations of the Agency;

2/ review and forward its proposals on policy matters relating to vehicle insurance against third party risks and studies on rates of premium and insurance fund tariff to be submitted pursuant to Article 4(4) and Article 23(2) of the Proclamation;

3/ issue directive on the collection and disbursement of the Insurance Fund;

4/ examine and decide cases of vehicle accident victims who complain for not being paid with the proper compensation in accordance with Article 20 of the Proclamation;

፭/ የፈንዱን ሂሳብ ኦዲት ያስደርጋል፤ የኦዲት ሪፖርቱን ይገመግማል፤ በሪፖርቱ መሠረት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፤

፮/ የኤጀንሲው የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶች፣ ዓመታዊ ፕሮግራሞችና በጀት ለመንግሥት ከመቅረባቸው በፊት ይገመግማል፤ ሲፈቀዱም አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

፯/ በኤጀንሲው በሚቀርቡለት የመድን ፈንድ አስተዳደርን በሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ይወስናል፡፡

## ፱. የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል፡፡

፪/ ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ያልፋል፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የአሠራር ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፲. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኤጀንሲውን ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ የተመለከቱትን የኤጀንሲውን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኤጀንሲውን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኤጀንሲውን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኤጀንሲውን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተገመገመ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ በመንግሥት ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤



5/ cause the accounts of the Insurance Fund to be audited; review the audit report and ensure that corrective measures are taken as recommended by the report;

6/ review the long and short term plans, annual programs and budget of the Agency before being presented to the government; and follow up the implementation of same upon approval;

7/ deliberate and decide on recommendations of the Agency on other issues relating to the administration of the Insurance Fund.

## 9. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet as frequently as its function requires.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Board are present at a meeting.

3/ The decisions of the Board shall be passed by a majority vote and, in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may adopt its own rules of procedure.

## 10. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Agency and shall, subject to the general direction of the Board, direct and administer the activities of the Agency.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Agency specified under Article 5 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Agency in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Agency, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and, upon review by the Board, submit to the Ministry the work program and annual budget of the Agency; and implement same upon approval by the government;

መ) ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

ረ) የኤጀንሲውን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ በቦርዱ ከተገመገመ በኋላ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኤጀንሲው ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኤጀንሲው ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## ፲፩. <u>በጀት</u>

የኤጀንሲው በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

## ፲፪. <u>የሂሳብ መዛግብት</u>

፩/ ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኤጀንሲው የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## ፲፫. <u>ስለመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

በተሽከርካሪ አደጋ ሦስተኛ ወገን መድን ዋስትና አዋጅ ቁጥር ፭፻፶፱/፪ሺ ተቋቁሞ የነበረው የመድን ፈንድ ጽሕፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በአዋጁ አንቀጽ ፴፪ መሠረት ለኤጀንሲው ተላልፈዋል፡፡

## ፲፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፰ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

d) effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Agency;

e) represent the Agency in its dealings with third parties;

f) prepare and, upon review by the Board, submit to the Ministry the activity and financial reports of the Agency.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Agency to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Agency.

## 11. <u>Budget</u>

The budget of the Agency shall be allocated by the government.

## 12. <u>Books of Account</u>

1/ The Agency shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Agency shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by him.

## 13. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>

The rights and obligations of the Office of the Insurance Fund established under the Vehicle Insurance Against Third Party Risks Proclamation No. 559/2008 are transferred to the Agency pursuant to Article 32 of the Proclamation.

## 14. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 6th day of January, 2014.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**